የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፲፯
አዲስ አበባ ጥር ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 17
ADDIS ABABA- 2nd February . 2004

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፪/፲፱፻፺፮ ዓ.ም

የኢትዮጵያ አቪዬሽን ሴኩሪት አዋጅ ...ገጽ ፪ሺ፱፻፹፭

CONTENTS

Proclamation No. 432/2004

Ethiopian Aviation Security Proclamation ...... Page 2985

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፪/፲፱፻፺፮

## የኢትዮጵያ የአቪዬሽን ሴኩሪት አዋጅ

በአየር ትራንስፖርት ደህንነት፣ አስተማማኝነትና ቅልጥፍና ላይ እየጨመረ የመጣውን የሕገ ወጥነት አደጋ መቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፣

ኢትዮጵያ የተቀበለችውን የቺካጎ ኮንቬንሽንና በአለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት የወጣውን የኮንቬንሽኑ አካል የሆነውን ተቀፅላ ፲፯ ተግባራዊ ማድረግ በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ አቪዬሽን ሴኩሪቲ አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፪/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

## PROCLAMATION NO. 432 /2004.

## ETHIOPIA AVIATION SECURITY PROCLAMATION

**WHEREAS**, it in necessary to counter the increasing threat of unlawful acts against the safety, regularity and efficiency of civil aviation;

**WHEREAS**, it is necessary to give effect to the Chicago Convention and annex 17 thereto issued by the International Civil Aviation Organization, to which Ethiopia is a party;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 (1) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows;

### Part One
### General

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Ethiopian Aviation Security Proclamation No. 432/2004."

**2. Definitions**

In this Proclamation, unless the context otherwise requires;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 4 40

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፩/ "ሕገወጥ ጣልቃ ገብነት" ማለት በበረራ ደህንነት ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች በወጣው አዋጅ ቁጥር ፴፩/፲፱፻፹፰ የተመለከተው ማናቸውም የወንጀል ድርጊት ነው፣

፪/ "አይሮፕላን" ማለት የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር ፪፻፸፫/፲፱፻፺፬ የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል፣

፫/ "ዛቻ" ማለት በፈንጂ ወይም በሌሎች አደገኛ ቁሳቁሶች የሚፈፀም በበረራ ወይም በመሬት ላይ በሚገኝ አይሮፕላን፣ በኤርፖርት አገልግሎት መስጫዎች ወይም በማንኛውም ግለሰብ ላይ ጉዳት እንደሚደርስ የሚገልጽ ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ ቢሆንም ባይሆንም በስም ወይም ያለስም የሚተላለፍ መረጃ ነው፣

፬/ "አደገኛ ቁሳቁስ" ማለት በአይሮፕላን የመንገደኞች ክፍልም ሆነ በጭነት ማስቀመጫ የአይሮፕላኑ ክፍል ውስጥ ቢጫን የመንገደኞችን ጤንነት እንዲሁም የመንገደኞችንና የአይሮፕላኑን ደህንነት ሥጋት ላይ የሚጥል ማንኛውም ዓይነት ቁሳቁስ ነው፣

፭/ "ዓለም አቀፍ ኤርፖርት" ማለት በዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት አባል አገራት ውስጥ በዓለም አቀፍ በረራዎች በመነሻነትና በመድረሻነት የሚያገለግልና በውስጡ የጉምሩክ፣ የኢሚግሬሽን፣ የጤና ጥበቃ፣ የእንስሳትና የእጽዋት ኳራንቲንና ሌሎች የቁጥጥር ተግባራት የሚካሄድበት ኤርፖርት ነው፣

፮/ "ኦፕሬተር" ማለት በአይሮፕላን አገልግሎት በመስጠት ወይም በአይሮፕላን አገልግሎት የሚሰጡትን በመርዳት ተግባር ላይ የተሰማራ ማንኛውም ግለሰብ፣ ድርጅት ወይም ኢንተርፕራይዝ ነው፣

፯/ "ፍተሻ" ማለት ሕገ-ወጥ ጣልቃገብነት ለመፈጸም የሚያገለግሉ መሣሪያዎችን፣ ፈንጅዎችን ወይም ሌሎች ቁሳቁሶችን ለይቶ ለማውጣትና ለማስቀ ረት በመፈተሻ መሣሪያዎች ወይም በእጅ የሚ ደረግ የሴኩሪቲ ቁጥጥር ነው፣

፰/ "ሴኩሪቲ" ማለት የቁጥጥር ስልቶችን፣ የሰው ኃይልንና ቁሳቁሶችን በማቀናጀት የሲቪል አቪዬ ሽን ሊደርስበት ከሚችል ማንኛውም ዓይነት ሕገ ወጥ ጣልቃገብነት የመከላከል ስራ ነው፣

፱/ "የሴኩሪቲ መፈተሻ መሣሪያ" ማለት የሲቪል አቪዬሽን እንዲሁም ፋሲሊቲዎቹን በተናጠል ወይም በተቀናጀ መልኩ ከሕገ-ወጥ ጣልቃ ገብነት ለመከላከል የሚያገለግል የመፈተሻ መሣሪያ ነው፣

1/ **"Acts of unlawful interference"** are the offences as described in the "Offences Against the Safety of Aviation, Proclamation No. 31/1996."

2/ **"Aircraft"** shall have the meaning provided in the "Ethiopian Civil aviation Authority Re-establishment Proclamation No. 273/2002."

3/ **"Threat"** shall mean a communicated threat, anonymous or otherwise, which suggests or infers whether true or false that the safety of an aircraft in flight or on the ground, or any airport or civil aviation facility or any person may be in danger from an explosive or other item or device.

4/ **"Dangerous Article"** shall mean any Article which is capable of posing risk to the passengers health and safety of the passengers as well as the aircraft when transported either in the cabin or in the cargo compartment.

5/ **"International Airport"** shall mean any airport designated within the Contracting State to service as a point of entry and departure for International flights and where controlling activates of customs, immigration, public health, animal and plant quarantine and others are carried out.

6/ **"Operator"** shall mean any person, organization or enterprise engaged in or assisting to those who are engaged in an aircraft operation.

7/ **"Screening"** shall mean the Security control to detect weapons, explosives dangerous Articles etc which may be used for committing an act of unlawful interference.

8/ **"Security** shall mean a combination of measured, human and material resources intended to safeguard civil aviation against acts of unlawful interference.

9/ **"Security Screening Equipment"** shall mean screening equipment, which prevents international civil aviation and its facilities from acts unlawful interference.

፲/ "የተከለከሉ ሥፍራዎች" ማለት ለሲቪል አቪዬሽን ሴኩሪቲ አመቺ አሠራር ሲባል መግቢያዎቻቸው በጥብቅ የተከለከሉ ወይም የሚጠበቁ በኤርፖርት የሚገኙ ሕንጻዎችን ፋሲሊቲዎች ናቸው፣

፲፩/ "የፀዳ ሥፍራ" ማለት በመንገደኞች የመፈተሻ ቦታና በአይሮፕላኑ መካከል የሚገኝና መግቢያው ጥብቅ ቁጥጥር የሚደረግበት ሥፍራ ነው፣

፲፪/ "የድንገተኛ ጊዜ እቅድ" ማለት በሕገወጥ ጣል ቃገብነት ወቅት የመንገደኞችን፣ የበረራ ሠራተ ኞችን፣ ከአይሮፕላን ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላ ቸው ሠራተኞችንና የኤርፖርቱ ማህበረሰብን ደህ ንነት ለማረጋገጥ የተለያዩ ድርጅቶችን ኃላፊ ነትና የሚወስዷቸውን እርምጃዎች የሚገልጽ እቅድ ነው፣

፲፫/ "ሚስጥራዊ ሰነዶች/ቁሳቁሶች" ማለት በሚመለከ ታቸው የመንግሥት አካላት ሚስጥር ተብለው የታወቁ ሰነዶች ወይም ቁሳቁሶች ናቸው::

## ክፍል ሁለት
## የኃላፊነት ድርድል

### ፫. የደህንነት ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን

፩/ የደህንነት ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥ ልጣን በተቋቋመበት ሕግ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የአቪዬሽን ሴኩሪቲ ሥራዎችን በበላይነት የማስፈፀም ሥልጣንና ተግባር በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የደህንነት፣ የኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ፣

ሀ/. ለሕገ-ወጥ ጣልቃ ገብነት አስፈላጊውን ምላሽ ይሰጣል፣ የኃይል እርምጃን ጨምሮ በበላይነት ይመራል፣ የማሳወቅ ተግባርን ይፈጽማል፣

ለ/ የሕገ-ወጥ ጣልቃገብነትን ለመከላከል የፍተሻ፣ የክትትል እና የአጀባ ተግባራትን ያከናውናል፣

ሐ/ በአገራዊና በኤርፖርት ደረጃ የድንገተኛ ጊዜ እቅድ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፣

10/ **"Restricted area"** shall mean those buildings and facilities located in the airport in which their access is seriously restricted for the purpose of convenient performance of international civil aviation security.

11/ **"Sterile area"** shall mean an area between any passenger inspection /screening station and an aircraft into which access in strictly controlled.

12/ **"Contingency plan"** shall mean a plan which indicates the responsibilities and action to be taken by various bodies to ensure the security of the passengers, flight personnel, ground personnel and the general public at the airport during an act of unlawful interference.

13/ **"Classified document/Articles"** shall mean documents or Articles which are known and classified by the concerned government agencies as secrete.

## Part two
## Assignment of Responsibilities

### 3. Security Immigration and Refugee Affairs Authority

1/ Without prejudice to the general responsibilities given to it under the law, the Security, Immigration and Refugee Affairs Authority Shall be responsible for the overall implementation of this Proclamation.

2/ Subject to Article 3.1.a. above, Security, Immigration and Refugee Affairs Authority Shall have the following duties and responsibilities with regard to aviation security: -

a) Respond to an act of unlawful interference, command the use of force;

b) Perform the activity of screening, surveillance and escorting to prevent acts of unlawful interference.

c) Develop and implement contingency plan at airport and national levels;

መ/ በአይሮፕላንና በአይሮፕላን ማረፊያ ጣቢያዎች ላይ የሚሰነዘሩትን አደጋ የመጣል ዛቻዎች ወይም እንቅስቃሴዎች እየተከታተለ ይገመግማል፣ መረጃዎችን እንደአስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸው አካሎችና አገሮች በማሰራጨት በሚወሰዱትም እርምጃዎች ላይ የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፣

ሠ/ የኤርፖርቶች፣ የአይሮፕላኖች፣ የኤርፖርት ፋሲሊቲዎች፣ የበረራ መረጃ መሣሪያዎችና የተከለከሉ ሥፍራዎች ጥበቃና የሴኩሪቲ ቁጥጥርን በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፣

ረ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ኃላፊነት የተሰጣ ቸው ወይም የሚመለከታቸው የተለያዩ መሥሪያ ቤቶችን ወይም ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ለማስተባበር የሚያስችል ስልት ይቀይሳል፣

ሰ/ የሚመለከታቸው አካላት በዚህ አዋጅ ተለይቶ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት መፈጸማቸውን ይከታተላል፣

ሸ/ ሕገ-ወጥ ጣልቃገብነት በሚፈጸምበት ወቅት ለመገናኛ ብዙኀን መግለጫ ይሰጣል፣ ከተለያዩ የዜና አገልግሎቶች ለሚቀርቡ ከአቪዬሽን ሴኩሪቲ ጋር የተዛመዱ ጥያቄዎች ምላሽና መግለጫ ይሰጣል፣

ቀ/ ከዚህ አዋጅ ጋር የተጣጣመ የኤርፖርት አቪዬሽን ሴኩሪቲ መመሪያ ያወጣል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣

በ/ የኤርፖርት አቪዬሽን ሴኩሪቲ መመሪያን በኃላፊነት የሚያስፈጽም የበላይ ኃላፊ ይሾማል፣

ተ/ የአንድ አገር አየር መንገድ ኦፕሬተር ልዩ የሴኩሪቲ ጥንቃቄ ሲጠይቅ በጥያቄው መሠረት አስፈላጊውን ጥንቃቄና ድጋፍ ያደርግለታል፣

ቸ/ በኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ላይ ሕገ-ወጥ ጣልቃ ገብነቶች ሲፈጸሙ ጥቃቶቹን ወይም ድርጊቶቹን አስመልክቶ የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ስለ ሪፖርት አቀራረብ ባወጣው ሥርዓት መሠረት ለድርጅቱ በጽሑፍ ሪፖርት ያቀርባል፣

d) Assess the threats or movements that pose danger on aircraft and airports. Transmit the information when necessary to and follow-up actions to be taken by relevant organization and countries;

e) Issue detailed directive regarding the protection and security control of airports, aircraft, airport facilities, navigational equipment;

f) Design a system to co-coordinate the activities of the various authorities or organizations responsible under this Proclamation;

g) Follow-up the implementation of the duties and responsibilities assigned to the relevant bodies in this Proclamation;

h) Inform the media about acts o unlawful interference; respond to questions raised from various media agencies regarding aviation security;

i) Issue and implement airport aviation security directive issued pursuant to this Proclamation;

j) Appoint airport security officer responsible for the implementation of airport aviation security directive;

k) Provide the required support to any country's airlines operator when it requests for special security measure;

l) Submit report to the International Civil Aviation Organization in accordance with the reporting procedure, when acts of unlawful interferences occur;

ኀ/ በየአገሮቹ ከሚገኙት የሲቪል አቪዬሽን ሴኩሪቲ አግባብ ያላቸው ባለሥልጣኖች ጋር ፈጣን እና አስተማማኝ የግንኙነት ሥርዓት ይዘረጋል፣

ነ/ በዓለም አቀፍ ኤርፖርቶች አዳዲስ ሕንፃዎች፣ መንገዶች ወይም ፋሲሊቲዎች ሲገነቡ ወይም የነበሩት ሲለወጡ ዲዛይኑ የአቪዬሽን ሴኩሪቲ እርምጃዎችን በበቂ ሁኔታ ለማስፈጸም በሚያስችል መልኩ መሆኑን አረጋግጦ ያጸድቃል፣

ኘ/ እንደአስፈላጊነቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሲቪል አቪዬሽን ሴኩሪቲን የሚመለከት ብሔራዊ ፖሊሲና ሕግ ያመነጫል፣ የፀደቀውን ፖሊሲና ህግ ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፣

አ/ የዚህን አዋጅ ውጤታማነት በቀጣይነት ለማረጋገጥ እንዲቻል በየወቅቱ መረጃዎችን ይመዝናል፣ የስኬታማነት መስፈርት በማዘጋጀትና በመገምገም ተገቢውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፣ ያስወስዳል፣

ከ/ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ኤርፖርቶች ለሚሰጡት የኤርፖርት ሴኩሪቲ አገልግሎቶች አስፈላጊ ድጋፍ ሰጪ መሣሪያዎችን እንዲሁም የስልጠና ፋሲሊቲዎችን ያሟላል፣

ኸ/ የአየር መንገድ ኦፐሬተሮችን የሴኩሪቲ መመሪያ ከዚህ አዋጅ አንፃር ይገመግማል፣ ያጸድቃል፣

ወ/ የኢትዮጵያ አቪዬሽን ሴኩሪቲ የሥልጠና ፕሮግራምና የሥልጠና መመዘኛ የአለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ያወጣውን ስታንዳርድ ጠብቆ ያዘጋጃል፣ ሥልጠና ይሰጣል፣ ተመሳሳይ ስልጠና የሚሰጡ ድርጅቶችን የሥልጠና ፕሮግራም ይዘት ገምግሞ ያጸድቃል፣ ከሌሎች አገሮችና ድርጅቶች ጋር የሥልጠና መረጃ ይለዋወጣል፣ ይተባበራል፣

ዐ/ የሴኩሪቲ መፈተሻ መሣሪያዎች በሚገዙበት ወቅት በተለይ የመንገደኛ ሻንጣዎች እና የሰውነት መፈተሻ መሣሪያዎች በአገሪቱ የወጣውን ደረጃ ያሟሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል::

## ፬. የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን

በዚህ አዋጅ መሠረት የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣

m) Establish reliable relations and fast communication with aviation security authority of other countries;

n) Ensure that architectural and infrastructure related requirements for the optimum utilization of aviation security measures are integrated into the design and construction of new facilities and alterations to existing facilities at air ports;

o) In collaboration with other relevant bodies, develop policy and law relating to civil aviation security and submit them for approval; notify the approved policy and law to the relevant bodies;

p) Evaluate regularly the continued effectiveness of this Proclamation by establishing evaluating criteria, reviewing and taking remedial actions;

q) Provide the required supporting facilities and training facilities of airport security services for airports in Ethiopia;

r) Based on this Proclamation, review and approve security programs or directives of air operators;

s) Develop Ethiopian aviation security training programme and training criteria in line with the standards issued by International Civil Aviation Organization, and provide training. Approve training programmes of other institutions; exchange information and cooperate with other countries and organizations that provide training;

t) Ensure that the procurement of aviation security equipment specially passenger baggage and physical screening equipment, meet the national standard;

## 4. Ethiopian Civil Aviation Authority

In accordance with this Proclamation, the Ethiopian Civil Aviation Authority shall have the following duties and responsibilities:

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን እየተከታተለ በአለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት በተቀመጠው ደረጃ መሠረት መሠራቱን ኦዲት ያደርጋል የአፈፃፀም ሪፖርቱን ለደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን፣ ለኢትዮጵያ የአቪዬሽን ሴኩሪቲ ኮሚቴና ለሌሎች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፣ በግኝቶቹ መሠረት የማስተካከያ እርምጃዎች በወቅቱ መወሰዳቸውን ያረጋግጣል፣

፪/ በኢትዮጵያ ውስጥ የተመዘገቡ የአየር መንገድ ኦፕሬተሮችንና የዓለም አቀፍ ኤርፖርቶችን የሴኩሪቲ መመሪያዎች ከዚህ አዋጅ ጋር በተጣጣመ መልኩ መቀረፃቸውን በመገምገም ለደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን አስተያየት ይሰጣል፣

፫/ የኢትዮጵያ አቪዬሽን ሴኩሪቲ የሥልጠና ፕሮግራም ይዘትንና የማሰልጠኛ ተቋማት የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ስለሥልጠና ያወጣቸውን ደረጃዎችና ተመራጭ ሃሳቦችን የጠበቁ ስለመሆናቸው ይቆጣጠራል፣

፬/ በየኤርፖርቶቹ በሚቋቋሙት የኤርፖርት ሴኩሪቲ ኮሚቴዎች ውስጥ በአባልነት ይሳተፋል፣

፭/ ሕገ-ወጥ ጣልቃገብነት የተፈጸመበት አይሮፕላን ባጋጠመ ጊዜ የማረፊያ ፈቃድና የኤር ናቪጌሽን አገልግሎት ይሰጣል::

## ፭. የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን

በሌሎች ሕጐች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣

፩/ የሲቪል አቪዬሽን ለበረራ ደህንነት የሚያገለግሉ ተቋሞችና መሣሪያዎች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ይመረምራል፣

፪/ በተለያዩ የጥበቃ ዘዴዎች የኤርፖርቶችን ክልል፣ ተርሚናሎችን፣ ለበረራ ደህንነት የሚያገለግሉ ተቋሞችንና መሣሪያዎችን ይጠብቃል፣

፫/ ለበረራ ደህንነት አገልግሎት የሚውሉ ተቋሞችና መሣሪያዎች ላይ ሊቃጣ የሚችል ዛቻና ለመከላከል የክትትል ተግባራት ያከናውናል፣

፬/ የበኩሉን የድንገተኛ ጊዜ እቅድ በማዘጋጀት በደህንነት፣ የኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ያስጸድቃል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፣

1/ Carryout performance auditing to ascertain that the responsible bodies have fulfilled the duties and responsibilities vested in them under this Proclamation, in accordance with the standard set by ICAO and forward the report thereon to Security, Immigration and Refugees Affairs Authority, Ethiopian Aviation Security Committee and to all other pertinent bodies; ensure that corrective actions are taken on time in accordance with the findings of the audit.

2/ Inform the Security, Immigration and Refugee Affairs Authority its evaluation of the aviation security programmes developed by operators and airports, in compliance with this Proclamation.

3/ Ensure the content of the Ethiopian aviation security training program and training institutions meet the standards and options of International Civil Aviation Organization.

4/ Participate as a member in all security committees by be established at airports.

5/ Give landing permission and air navigation services to an aircraft under an act of unlawful interference.

## 5. The Federal Police Commission

Without prejudice to the power given it under the law, the Federal Police Commission shall have the following duties and responsibilities;

1/ Investigate crimes committed on civil aviation institutions and equipment flight safety equipments.

2/ Protect airport areas, terminals, institutions and flight safety equipments.

3/ Perform surveillance activities to prevent unlawful acts against aviation institutions and flight safety equipment.

4/ Prepare contingency plan to be approved by Security Immigration and Refugee Affairs Authority and implement it upon approval.

፮. የአገር መከላከያ ሚኒስቴር

በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፣

፩/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በድንገተኛ ጊዜ ዕቅድ መሠረት ይሳተፋል፣

፪/ የመከላከያ ኃይል የሲቪል ኤርፖርቶች የጋራ ተጠቃሚ ሲሆን የመተላለፊያ በሮችን በመቆጣጠርና በሌሎች የሴኩሪቲ ተግባሮች ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ጋር ይሳተፋል::

፯. የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት

በተቋቋመበት ሕግ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት፣

፩/ በኤርፖርቶች አቪዬሽን ሴኩሪቲ መመሪያ ዝግጅት እና ተግባራዊነት ላይ ይሳተፋል፣

፪/ በኤርፖርት አቪዬሽን ሴኩሪቲ ኮሚቴ ውስጥ በአባልነት ይሳተፋል፣

፫/ የአዲስ ኤርፖርት ግንባታ ወይንም የነበረውን ለማሻሻል የግንባታ ሥራ ሲከናወን ዲዛይኑ የአቪዬሽን ሴኩሪቲን ፍላጐት ያገናዘበ ወይንም ያሟላ መሆኑን አረጋግጦ ለደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን አቅርቦ ያስጸድቃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣

፬ የደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የኤርፖርት የድንገተኛ ጊዜ እቅድ ያዘጋጃል፣

፭/ የኤርፖርት ፋሲሊቴሽን መመሪያና ልዩ ልዩ የአሰራር ሥርዓቶች በሚያዘጋጅበትና ተግባራዊ በሚያደርግበት ወቅት ይህን አዋጅ መከተሉን ያረጋግጣል::

፰. ኦፕሬተር

ማናቸውም ኦፕሬተር ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡትን መመሪያዎች ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለበት::

፱. የኢትዮጵያ የሲቪል አቪዬሽን ሴኩሪቲ ኮሚቴ

፩/ የኢትዮጵያ የሲቪል አቪዬሽን ሴኩሪቲ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::

፪/ ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፣

**6. Ministry of Defense**

a) Without prejudice to the power given to it under the law, the Ministry shall participate in the execution of the contingency plan, where necessary.

b) Provide access control and perform other security functions jointly with the Police at civil airports.

**7. Ethiopian Airports Enterprise**

without prejudice to the responsibilities vested to it by law, the Ethiopian Airports Enterprise shall have the following duties and responsibilities:

1/ Participate in the preparation and implementation of an airports' aviation security directive:

2/ Participate as a member in the airport security committee.

3/ Ensure that the design of new airport construction or rehabilitation meets the requirements of aviation security by submitting the design for approval to the Security, Immigration and Refugee affairs Authority.

4/ Develop contingency plan in accordance with directives issued by Security, Immigration and Refugees Affairs Authority.

5/ Ensure that this Proclamation is complied with when preparing airport facilitation directive and various working rules.

**8. Operator**

Any operator shall implement this Proclamation and the directive issued here-under.

**9. The Ethiopian Civil Aviation Security Committee**

1/ There is hereby established the Ethiopian Civil Aviation Security Committee

2/ The Committee shall have the following members;

ሀ/ የደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ............................ ሰብሳቢ
ለ/ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ............ ፀሐፊ
ሐ/ የገቢዎች ሚኒስቴር .................. አባል
መ/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ............ አባል
ሠ/ የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን .......................................... አባል
ረ /የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት ... አባል
ሰ/ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ኢንተርፕራይዝ .................................. አባል

፫/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኮሚቴው ተጨማሪ አባላትን ከሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ባለሙያዎችን በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት እንደአስፈላጊነቱ ሊያሳትፍ ይችላል::

፬/ የኮሚቴ አባል የሆነ እያንዳንንዱ መሠሪያ ቤት ወይም ድርጅት በበላይ ኃላፊው ወይም በምክትሉ ይወከላል::

፭/ የኢትዮጵያ ሲቪል የአቪዬሽን ሴኩሪቲ ኮሚቴ፣

ሀ/ በሲቪል አቪዬሽንና በአገልግሎት መስጫዎቹ ላይ ሊኖሩ የሚችሉ ስጋቶችን ለመከላከል መወሰድ የሚገባውን የአቪዬሽን ሴኩሪቲ እርምጃ አስመልክቶ የደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣንን ያማክራል፣

ለ/ ታምኖባቸው ተግባራዊ የሆኑትን ዕርምጃዎች አፈፃፀምና በየወቅቱ እየተለዋወጡ የሚመጡ አዳዲስ ስጋቶችን ይገመግማል፣ በአቪዬሽን ሴኩሪቲ መስክ የታዩትን የቴክኖሎጂ ለውጦች የተሻሻሉትን የቴክኖሎጂ ግኝቶችንና ሌሎችንም ባጠቃላይ እየገመገመ ድክመት በታየባቸው ጉዳዮች ላይ የማሻሻያ የውሣኔ ሃሳብ ያቀርባል፣

ሐ/ አቪዬሽን ሴኩሪቲን በሚመለከት ኃላፊነት የተጣለባቸው ድርጅቶችና ወኪሎቻቸው በየጊዜው የሚከሰቱትን ስጋቶች ለመቋቋም በመካከላቸው ቅንጅታዊ አሠራር መኖሩን ያረጋግጣል፣

መ/ የዚህ አዋጅ የማሻሻያ ሃሳቦችን ይመረምራል፣ እንዲጸድቅም የማሻሻያ ውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣

ሠ/ በኤርፖርት የሲቪል አቪዬሽን ሴኩሪቲ ኮሚቴ የሚቀረቡትን የማሻሻያ ሐሳቦች ይመረምራል፣ ለደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል:

፮/ ኮሚቴው የራሱን የአሠራር መመሪያ ያወጣል::

a) Security, Immigration and Refugee Affairs Authority............................ Chairman
b) Federal Police Commission...... Secretary
c) Ministry of Inland Revenue....... Member
d) Ministry of Foreign Affairs....... "
e) Ethiopian Civil Aviation Authority "
f) Ethiopian Airports Enterprise....... "
g) Ethiopian Airlines Enterprise......... "

3/ The Committee may, where necessary allow the participation of additional members from government and non-government organizations, temporarily or permanently.

4/ Each committee member, governmental and non-governmental shall be represented by the high official or the deputy thereof.

5/ The committee shall:

a) Advise the Security, Immigration and Refugee Affairs Authority regarding the measures to be taken against the possible threats on civil aviation and the facilities.

b) Review the already implemented measures and new threats and submit proposals of change taking into account technological developments and other factors.

c) Ensure the existing of among the organizations and their representatives that coordination of implementation are responsible to implement these Regulations.

d) Review amendment proposals of these Regulations and submits opinions thereon

e) Review proposals submitted by airport aviation security committee, and opinion thereon Submits to security Immigration and Refugee Affair Authority.

6/ The committee develops its internal working rules.

## ፲. የኤርፖርት አቪዬሽን ሴኩሪቲ ኮሚቴ

፩/ የኤርፖርት አቪዬሽን ሴኩሪቲ ኮሚቴ የዓለም አቀፍ አገልግሎት በሚሰጡ ኤርፖርቶች እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ኤርፖርቶችም ይቋቋማል::

፪/ የኤርፖርት አቪዬሽን ሴኩሪቲ ኮሚቴ፣

ሀ/ የአቪዬሽን ሴኩሪቲ እንዲጠናከር የደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣንን ያማክራል፣

ለ/ በኤርፖርት ላይ የሚከናወኑትን የሴኩሪቲ እርምጃዎችና የአሰራር ሥርዓቶችን በተቀናጀ መልኩ ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል::

## ክፍል ሦስት
## በሰዎችና ወደ አይሮፕላን በሚጫኑ እቃዎች ላይ የሚደረግ ቁጥጥር

## ፲፩. ስለፍተሻ አስፈላጊነት

፩/ ማንኛውም መንገደኛም ሆነ የመንገደኛ ዕቃ ወደ አይሮፕላን ወይም በፍተሻ ወደ ጸዳው የመን ገደኞች መቆያ ስፍራ ከመግባቱ በፊት መፈተሽ አለበት::

፪/ የበረራ ሠራተኞች፣ የኤርፖርትና የአቪዬሽን ሠራተኞችን ሌሎች ሰዎች ከመፈተሻ ቦታው ወደ ጸዳው ሥፍራ ከማለፋቸው በፊት እንደመንገደኞች ሁሉ ይፈተሻሉ:: ፍተሻውም የእጅ ሻንጣን ያጠቃልላል::

፫/ አይሮፕላን፣ አይሮፕላን ላይ የሚጫን ዕቃ፣ የፈጣን መልዕክት ጥቅልና ፖስታ የሴኩሪቲ ቁጥጥር ወይም ተገቢው ፍተሻ ይደረግበታል::

## ፲፪. ልዩ የፍተሻ ሥርዓት

፩/ የዲፕሎማቶች፣ የዲፕሎማቲክ ፖውችና የዲፕ ሎማቶች ሻንጣዎች አፈታተሽን በሚመለከት ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ ለማድረግ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ይፈጸማል::

፪/ ሚስጥርነታቸው እንደተጠበቀ በመንግሥት የሚጓጓዙ ዕቃዎች የሚፈተሹት ከማንኛውም መሣሪያዎችና አደገኛ ቁሳቁሶች ነፃ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ብቻ ነው:: ነገር ግን አጠራጣሪ ወይም ምንነቱ በትክክል ያልታወቀ ነገር ሚስጥራዊነት ባላቸው ቁሳቁሶች ውስጥ ቢገኝ በማንኛውም ኦፕሬተር መጓጓዝ አይኖርባቸውም::

## 10. Airport Aviation Security Committee

1/ The committee shall be established at international airports as well as at domestic airports as required.

2/ The committee shall:

a) Advise the Security, Immigration and Refugee Affairs Authority on the strengthening of aviation security.

b) Ensure that the security measures and procedures thereof at airports are implemented in a coordinated manner.

## PART THREE
## Security Control of Persons and Items Going on Board Aircraft

## 11. Requirement of Screening

1/ Any passenger and his baggage shall be screened before entering into an aircraft or sterile area.

2/ Airline crew, airport staff and other non-passengers passing through the security point into the sterile area shall be screened in the same manner as passengers. The screening shall include carry-on baggage.

3/ The aircraft, all cargo, courier and express parcels, and mail shall be subject to appropriate security control or screening.

## 12. Special Screening Procedures

### 1/ Diplomats and Diplomatic Pouch

The screening of Diplomats, Diplomatic Pouches and Diplomatic baggage shall be carried out in accordance with the directives issued by Ministry of Foreign Affairs for the implementation of International Agreements to which Ethiopia is a party.

### 2/ Classified Materials

Materials that are classified by appropriate agencies of government shall be inspected only to the extent necessary to ensure the absence of weapons or dangerous articles. However, if any suspicious or unidentified material is found within the classified material, it shall not be transported by any operator.

## ፲፫. ከፍተሻ ነፃ ስለመሆን

፩/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስፈላጊውን የተለየ ሁኔታ ለማመቻቸት እንዲቻል ከፍተሻ ነፃ የሆኑ ሰዎች የጉዞ መረጃ ለደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣንና ለአየር መንገድ ኦፕሬተሮች አስቀድሞ ይገልፃል::

፪/ መንግሥት መፈተሻ አይገባቸውም ብሎ አስቀድሞ የወሰነላቸው ግለሰቦች ከፍተሻ ነፃ ሊሆኑ ይችላሉ::

## ፲፬. በግል ፍተሻ ስለሚደረግበት ሁኔታ

ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው እቃዎች የያዙ፣ የልብ ምት ማስተካከያ መሣሪያ የተገጠመላቸው፣ የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ወይም ሌሎች የግል ፍተሻ የሚያስፈልጋቸው መንገደኞች በግል ከሌሎች መንገደኞች እይታ በተከለለ ሥፍራ ሊፈተሹ ይችላሉ::

## ፲፭. የተፈቀደ የጦር መሣሪያ ስለማጓጓዝ

የሕግ አስከባሪ ሠራተኛ ወይም ሌላ ሕጋዊ ፍቃድ ያለው ሰው በአይሮፕላኑ የመንገደኞች ክፍል ወይም ሻንጣ ውስጥ የጦር መሣሪያ ይዞ ሊጓዝ ይችላል::

## ፲፮. በጥበቃ ወይም በአስተዳደራዊ ቁጥጥር ሥር የዋለ ሰው ስለማጓጓዝ

፩/ በጥበቃ ወይም በአስተዳደራዊ ቁጥጥር ሥር የዋለ ሰው ወይም አእምሮው የታወከ መንገደኛ ስለሚጓጓዝበት ወይም ወደ መጣበት አገር ስለሚመለስበት ሁኔታ አጓጓዡ ወይም የሚመለከተው አገር ቅድሚያ እንዲያውቀው ይደረጋል::

፪/ የአየር መንገድ ኦፕሬተሮች በሕግ ጥላ ሥር ሆኖ የሚጓዝ መንገደኛን ደህንነት ለማረጋገጥ ሲባል ያለውን ሕግ መሠረት አድርገው የአጓጓዝ ሥርዓቱን በየራሳቸው የሴኩሪቲ መመሪያ ውስጥ በዝርዝር ማስቀመጥ አለባቸው::

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፲፯. የአቪዬሽን ሴኩሪቲ ወጪ አሸፋፈን

፩/ በዚህ አዋጅ የአቪዬሽን ሴኩሪቲን ለማስፈጸም ሥልጣን የተሰጠው አካል ወጪዎችን በሚመለከት ከመደበኛ ከደመወዝና ሌሎች የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች በስተቀር የፋሲሊቲዎች ግዢ፣ ጥገናና ተያያዥ ወጪዎች እንዲሁም ተፈላጊ የግንባታ ሥራዎች በሙሉ ለሚያስተዳድራቸው ኤርፖርቶች በኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት ይሸፈናል::

## 13. Exemption from screening

1/ For the purpose of special arrangement, the Ministry of Foreign Affairs shall forward ahead of time the traveling information of those persons exempted from screening process, the Security, Immigration and Refugee Affairs Authority and operators.

2/ Persons may be exempted by the Government with prior notification.

## 14. Private Screening

Passengers carrying high value goods, those with pacemakers, those who are handicapped or others requiring private screening, shall be screened on a protected area.

## 15. Authorized Carriage of Weapons

Law enforcement personals or any legally licensed person may carry weapons in the cabin or baggage compartment of the aircraft.

## 16. Carriage of Persons in Custody or Administrative Control

1/ The operator or the relevant Country shall be given prior notification of the conditions of carriage of a person in custody or administrative control or mentally interdicted. The directive on the details shall be issued by Security, Immigration and Refugee Affairs Authority.

2/ In order to ensure the security of the passenger who is under legal custody, operators shall incorporate procedures in their respective aviation security program,.

## PART FOUR
## Miscellaneous Provisions

## 17. Civil Aviation Security Expense

1/ The Ethiopian Airports Enterprise, except for the salaries of security personnel and operational expenses, shall bear the expenditure to procure facilitation materials and to carry out required construction works in all airports under it administration, required for Civil Aviation security.

፪/ ድርጅቱ ያወጣውን ወጪ የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ተመራጭ ሃሳቦችን ተከትሎ ከተጠቃሚዎች ሊተካ ይችላል::

፲፰. <u>መመሪያ ስለማውጣት</u>

ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን መመሪያ ለማውጣት ይችላል::

፲፱. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ሕጎች፣ መመሪያዎችና የአሠራር ልምዶች በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖራቸውም::

፳. <u>ቅጣት</u>

ይህን አዋጅ ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ይቀጣል::

፳፩. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥር 25 ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ጥር 25 ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2/ The expenditure made by the Enterprise shall be reimbursed from users in accordance with the International Civil Aviation Organizations recommended practices.

**18. Authority To Issue Directives**

The Security, Immigration and Refugee Affairs Authority may issue directives for the implementation of this Proclamation.

**19. Inapplicable Laws**

For matters provided herein, laws directives and practices that contravene this Proclamation shall be inapplicable.

**20. Penalty**

Any one who contravenes this Proclamation shall be punished in accordance with the relevant law.

**21. Effective Date**

This Proclamation shall come into force as of 2nd day of February, 2005.

**Done at Addis Ababa, this 2nd day of February, 2004.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**